የሰበር መ/ቁ 227293

ጥቅምት 02 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

በእውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- ወ/ሮ የትፈንታ ምስክር ጠ/አስራት ሰብስቤ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ደመቀ ጎሹ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 80361 በቀን 21/06/2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 288090 በቀን 02/09/2014 ዓ.ም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዙ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት በቀን 26/11/2013 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረቡት ክስ ከሟች ባለቤቴ አቶ ግርማ ወዳጆ የጋራ ሀብት የሆነ በጉ/ክ/ከ/ወ-7/ የቤት ቁጥር አዲስ የሆነው ቤት ተጠሪ በቀን 18/10/2000 ዓ.ም ውክልና በመውሰድ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ንብረቱን ሲያተዳድር

የቆየ ቢሆንም ህግ በመጣሱ ዉክልናዉ በቀን 01/12/2005 ዓ.ም ተነስቷል፣ተጠሪ የተከራየውን ቤት ውዝፍ ኪራይ ከፍሎ ቤቱን እንዲለቅ በመ/ቁ 53640 ክስ አቅርቤ ፍ/ቤቱ የሽያጭ ውል ስላለ ተጠሪ ቤቱን ሊለቅም ሆነ የቤት ኪራይ ሊከፍል አይገባም በማለት የወሰነ በመሆኑ እና የሽያጭ ውል መኖሩን ያወኩት በዚህ ውሳኔ በመሆኑ አመልካች እና ባለቤቴ የሸጥነው ቤት የለም፣አመልካች በሽተኛ እና ማንበብ አለመቻሌን ተጠቅሞ ተጠሪ ከቅን ልቦና ውጭ ያዘጋጀው የሽያጭ ሰነድ በመሆኑ በውሉ ላይ ፊርማ ያልፈረምኩ እና ገንዘብ ያልተቀበልኩ፣ውሉም ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መከላከያ መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተያዘዉ በኪራይ ሳይሆን በሽያጭ መሆኑ በመ/ቁ 53640 ላይ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፣አመልካች ከዚህ ቀደም የሽያጭ ውል እንደሌለ ክስ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ አሁን በድጋሚ የቀረበ ክስ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፣ክሱ በበቂ ምክንያት እና ማስረጃ የተደገፈ አይደለም፣ አመልካች ሙሉ ጤንነት እንደነበራቸው ከዚህ ቀደም በተደረገ ክርክር የተረጋገጠ በመሆኑ እና አሁንም ሊረጋገጥ የሚችል ነው በሚል ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማስረጃ ሰምቶና አመዛዝኖ አመልካች ባቀረቡት ማስረጃዎች ውል አለመዋዋላቸውን አላረጋገጡም፣ውሉ በሚመለከተው አካል ፊት አልተደረገም ረቂቅ ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንጂ በተዋዋይ ወገንና በ3ኛ ወገን መካከል ባለመሆኑ የአመልካች ክርክር የህግ መሰረት የለውም በማለት ውሉ ሊፈርስ አይገባም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የተካደ እና በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 መሰረት እንደረቂቅ የሚቆጠር ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ዉሉ ሊፈርስ አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፣ሰነዱ ሀሰተኛ ነው በሚል ተከራክረን ምስክሮች በሰጡት ቃል አመልካች ሲፈርሙ ያላዩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ፊርማው የአመልካች መሆኑና

አለመሆኑ በፎሬንሲክ ሳይረጋገጥ የስር ፍ/ቤት ውሉ አይፈርስም በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት በመሆኑ ዉሳኔዉ እንዲታረም በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል የሌለ መሆኑን በመግለጽ በተከራከሩበት ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የወሰነበት አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ክርክር የተነሳበት ቤት በተመለከተ ውዝፍ ኪራይ ከፍሎ ቤቱን ይልቀቅልኝ በማለት አመልካች በመ/ቁ 53640 ክስ አቅርበው ቤቱን ገዝቼ የምገለገልበት መሆኑ ተረጋግጦ ክሱ ውድቅ ሲደረግ ዉሳኔዉ እስከ በላይ ፍርድ ቤት ደርሶ ፀድቋል፤ለ2ኛ ጊዜ በመ/ቁ 284696 ባቀረቡት ክስ ተከሳሾች የነበሩት ተጠሪ፣የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደርን እና የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ደንብ ማስከበር ጽ/ቤትን ሁከት ፈጥረዋል እና ሁከት ይወገድልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዉ ፍ/ቤቱ ሁከት የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፤በህግ ማሽነፍ ሲያቅታቸው የሸጡልኝን ቤት አጥሩን በሃይል በማፍረስ በመያዛቸው ሁከት እንዲወገድ በመ/ቁ79940 ክስ አቅርቤ ሁከት እንዲወገድ በተሰጠ ውሳኔ መሰረት ቤቱን በድጋሚ ተረክቤ እየተገለገልኩ እገኛለሁ፤በመሆኑም የአሁኑ ክርክር ለ4ኛ ጊዜ የቀረበ በመሆኑ መዝገቦችን በመመልከት ክሱን ውድቅ እንዲያደርግልኝ አመልካች የጤና ችግር ያለባቸው መሆኑን በመግለጽ የቤት ሽያጭ ስምምነት እንዳላደረጉ በማስመሰል ያቀረቡት ክርክር ሀሰት ነው፤ሽያጩን አድርገው ውሃና መብራት ለማስገባት ውክልና ሲሰጡኝ እሳቸውም ሆኑ ሚች ባለቤታቸው በወቅቱ የመንግስት ሰራተኞች ነበሩ፤አመልካች የቤት ሽያጭ ውል የፈረሙ መሆኑን በመ/ቁ53640 ላይ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በመጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በቀን 05/11/2014ዓ.ም የተጻፈ መስቀለኛ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን አጭር ይዘቱም አመልካች እና ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በመ/ቁ 53640፣ 284696 እና 79940 ክርክር አድርገን አሁን ለ4ኛ ጊዜ የቀረበ ክስ በመሆኑ ይህም ሊሆን የቻለው በቂ ወጪና ኪሳራ ስለማይቆረጥ አመልካች ምክንያት እየቀያየሩ ክስ እያቀረቡብኝ ከመሆኑም ባሻገር በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 እና 244(2)(ለ) መሰረት ክሱ ውድቅ ሊደረግ እንደሚገባ ያቀረብኩት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መታለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤የሽያጭ ውሉ የተደረገው ነሐሴ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ሲሆን የውል ይፍረስልኝ ክስ የቀረበው ከ12 ዓመት በኋላ በመሆኑ ይርጋ ያግደዋል በማለት ያቀረብኩት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መታለፉ መሰረታዊ የህግ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ሰበር ችሎቱ ሰኔ 22 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት መስቀለኛ አቤቱታዉን መርምሮ ተጠሪ ያቀረቡት ይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ መደረጉ በአግባብ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን በጭብጥነት በመያዝ መስቀለኛ ተጠሪ(አመልካች) መልስ እንዲሰጡበት አዟል፡፡መስቀለኛ ተጠሪ (አመልካች) ባቀረቡት መልስ በስር ፍ/ቤት የቤት ሽያጭ ውሉ በፎሬንሲክ እንዲመረመር ተደርጎ ምላሽ ባይሰጠውም ዉሉ በመስቀለኛ መልስ ሰጭ (በአመልካች) የሚታወቅ አይደለም፤በስር ፍ/ቤት ያቀረብኩት የውል ይፍረስልኝ አቤቱታ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1810 መሰረት በ2 ዓመት ይርጋ የሚገደብ ሳይሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት 10 ዓመት ይርጋ ጊዜ የሚታይ ነው፡ሰበር ችሎት በመ/ቁ 48012 (ቅጽ 12) እና 131151 (ቅጽ 22) ላይ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ሀሰተኛ የሽያጭ ውል መኖሩን ያወኩት በመ/ቁ 53640 ስንከራከር መስቀለኛ አመልካች ካቀረበው ሰነድ ነው፤ፍ/ቤቱ አከራክሮ ውሳኔ የሰጠዉ በ3/05/2011 ዓ.ም በመሆኑ ውል ይፍረስልኝ የሚል ክስ ያቀረብኩት በ25/01/2013 ሲሆን ክሱን ያሻሻልኩት ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም በመሆኑ 10 ዓመት አልሞላውም በማለት ይርጋ አያግደውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ የመልስ መልስ በማቅረብ የመስቀለኛ ይግባኝ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎችን አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ክሱ በይርጋ መታገዱን እንዲሁም ዳግም የቀረበ ክስ ነዉ በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማቅረቡን መዝገቡ ያሣያል፡፡በቀዳሚነት ምላሽ ማግኘት ያለበት ጭብጥ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት ተጠሪ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ መደረጉ ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነዉ፡፡ይርጋ ደንብ መብት ለማስከበር የሚቀርብ ክስ /limitation of action/ ቀሪ የማድረግ ዉጤት ያለዉ የህግ ጽንሰ ሃሳብ ነዉ፡፡የይርጋ ደንብ /period of limitation/ ዓይነተኛ ዓላማ አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ባለመብት በህጉ በተገለጸ የጊዜ ገደብ ዉስጥ በመብቱ ባለመስራቱ የመብት ጥያቄዉ በጊዜ ማለፍ ምክንያት ቀሪ የሚሆንበት በሌላ በኩል ግዴታ ያለበትን ወገን ግዴታዉን እንዲፈጽም ከሚቀርብበት ክስ ነጻ የማድረግ ዉጤት ያለዉ ነዉ፡፡የይርጋ ጊዜ እርዝማኔ እንደጉዳዩ ዓይነትና ባሕርይ የሚለያይ ስለመሆኑ የይርጋ ደንብ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ስለዚህም ተፈጻሚነት ያለዉ ይርጋ ጊዜ ለመለየት የሚቻለዉ የተጠየቀዉ ዳኝነት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ዓይነት ወይም የክስ ምክንያት እና በመብቱ መስራት የሚቻልበትን ጊዜ በሚመለከት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉን ህግ መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

በመሰረቱ ዉል በተዋዋይ ወገኖች መካከል መብትና ግዴታ ሊፈጥር በህግ አስገዳጅነት የሚኖረዉ ስለዉል አመሰራረት በህግ የተደነገጉትን ሁኔታዎች አሟልቶ የተደረገ መሆኑን ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ይኸዉም ተዋዋዮቹ ለመዋዋል ችሎታ ያላቸዉ ሰዎች መሆኑን፣በነጻ ፈቃዳቸዉ ያደረጉት መሆኑን፣የዉለታዉ ጉዳይ የሚቻልና ህጋዊ የሆነ መሆኑን እና በህግ የተደነገገዉን የዉል አጻጻፍ ስርዓት(ፎርም) ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1678 ይመለከቷል)፡፡በህጉ የተደነገገዉን የዉል አመሰራረት መስፈረትና ስርዓት አሟልቶ የተደረገ ዉል ህግ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖችን የሚያስገድድ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1731(1) ድንጋጌ ይዘት ያሥገነዝባል፡፡ሆኖም ዉሉ አመሰራረት ላይ ጉድለት አለበት ወይም በአፈጻጸም ሂደት በተከሰተ ሁኔታ ዉል እንዳይፈጸም ያደረገ እንደሆነ ከተዋዋዮቹ አንዱ ወይም ጥቅም ያለዉ ሶስተኛ ወገን ዉሉ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ ጥያቄ ሊነሳበት ይችላል፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች ይመለከቷል)፡፡ ዉል የማፍረስ /invalidation/ መነሻ ምክንያቶች በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808 ስር ተዘርዝረዋል፡፡እነዚህም ውል አመሠራረት ላይ የፈቃድ ጉድለት መኖር፤ ከተዋዋይ ወገኖች ችሎታ ማጣት፤ የውለታው ጉዳይ ህገወጥነት ወይም ኢሞራላዊነት ወይም የውሉ አቀራረጽ /ፎርም/ በህግ የተደነገገውን ሥርዓት አለመጠበቅ የሚሉ ናቸው፡፡ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላው መነሻ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ በማንና መቼ መቅረብ እንዳለበትም በህጉ ተመልክቷል፡፡ዉል እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ የሚቀርብ ክስ ይርጋ ጊዜ ዉሉን ለማስፈረስ ወይም ለማሰረዝ እንደቀረበዉ ምክንያት እና ሁኔታ በሁለት ዓመት ወይም በአስር ዓመት ጊዜ የተገደበ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1810 እና 1845 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ነሐሴ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ሲሆን ክሱ የቀረበዉ በ25/01/2013ዓ.ም መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ ዉሉን አላዉቀዉም፣አልፈረምኩም፣ስምምነት አልሰጠሁም በተጨማሪም ማንበብና መጻፍ ስለማልችል ፊርማ የእኔ አይደለም በማለት ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቃቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ ክርክራቸዉ በሁለት ዘንግ የተከፈለ መሆኑን ነዉ፡፡ይኸዉም በአንድ በኩል ተዋዋይ እንዳልሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ዉሉን አድርገዋል ቢባል እንኳን የኪራይ እንጂ የሽያጭ ስምምነት አላደረኩም ሽያጭ የተባለዉ ሰነድ በሀሰት የተዘጋጀ ዉል ነዉ የሚል ነዉ፡፡ተዋዋይ አይደለሁም፣የሽያጭ ዉል መኖሩን ያወቅኩት ኪራይ ዉል ምክንያት በቀረበዉ ክስ ነዉ የሚለዉን በተመለከተ ተጠሪ ክስ እንዲያቀርቡ የሚጠበቀዉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመብታቸዉ መስራት ከሚችሉበት ማለትም የሽያጭ ዉል መኖሩን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን የፈቃድ ጉድለትን መነሻ ያደረገ ዉል ማፍረሻ ምክንያት መሰረት ተድረጎ ሲታይ በሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1846 እና 1810(2) ይመለከቷል፡፡ነገር ግን የተባለዉ የዉል ሰነድ ሀሰተኛ ነዉ የሚለዉ የዉሉን ህጋዊነት የሚመለከት እንደመሆኑ ዉሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ዉስጥ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤት ይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ ያደረገዉ ተጠሪ ዉሉ እንዲፈርስ የጠየቁት በሀሰት የተዘጋጀ ነዉ በሚል ምክንያት በመሆኑና ይህንንም ያወቁት በኪራይ ዉል ክርክር በ2008ዓ.ም በመሆኑ አስር ዓመት ጊዜ አላለፈበትም በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ በቀን 15/02/2014ዓ.ም የሰጠዉ ብይን ይዘት ያሣያል፡፡ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ብይን ይዘት እና በመጨረሻም የሰጠዉ ፍርድ ይዘት እንደሚያሣን ተጠሪ ቤቱን የያዘዉ በኪራይ ሳይሆን በሽያጭ ዉል ስለመሆኑ የምስክሮች ቃል መሰረት ተድረጎ በመ/ቁ/ 53640 ላይ ከመወሰኑም በተጨማሪ ሽያጭ ዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ የአመልካች መሆኑም ጭምር በፎረንሲክ ምርምራ ጭምር የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡ስለዚህም ነሐሴ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገዉን የቤት ሽያጭ አላዉቅም ፤አልፈረምኩም ፤ሀሰተኛ ሰነድ ነዉ ቢሉም ዉሉ ላይ አመልካች የፈረሙ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር በመሆኑ ዉሉ መኖሩን ያወቁት በ2008ዓ.ም ነዉ የሚለዉ የአመልካች ክርክር በማስረጃ የተስተባበለ መሆኑን ያሣያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ለይርጋ አቆጣጠር መነሻ ተደርጎ የሚወሰደዉ ዉሉ የተደረገበት 21/12/2000ዓ.ምእንጂ2008ዓ.ምአይደለም፡፡ዉሉ ከተደረገበት 21/12/2000ዓ.ም ክሱ እስከቀረበበት 25/01/2013 ዓ.ም ያለዉ ጊዜ ሲታሰብ ከአስር ዓመት በላይ ነዉ፡፡ክሱ የቀረበዉ አስር ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1845 መሰረት ይርጋ ጊዜ ገደብ የታገደ ነዉ፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ክሱ ይርጋ ጊዜ አላለፈበትም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በክርክሩ የተረጋገጠዉን ፍሬነገር ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ክሱ ከጅምሩም በይርጋ ቀሪ መደረግ የነበረበት በመሆኑ ሌሎች በተጠሪ በኩል የተነሱትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችም ሆነ በፍርዱ ላይ በአመልካች በኩል የቀረበዉን አቤቱታ መመርመር አስፈላጊ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በቀን 21/12/2000ዓ.ም የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ ክስ የቀረበዉ አስር ዓመት ይርጋ ጊዜ ያለፈበት ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ ማድረግ በፍሬነገሩ ገብቶ የሰጠዉ ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የተጠሪን መስቀለኛ አቤቱታ መሰረት በማድረግ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የስር ፍርድ ቤት ብይን እና ዉሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ለ) እና 10(1/ሀ) መሰረት በማረም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ዉሳኔ**

1ኛ/የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ80361 ላይ በቀን15/02/2014ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና በቀን 21/06/2014ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/288090 ላይ በቀን 02/09/2014ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/በ21/12/2000ዓ.ም የተደረገ ዉል እንዲፈርስ አመልካች ያቀረቡት ክስ አስር ዓመት ይርጋ ጊዜ አልፎበታል፡፡

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉ ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፤

**ትእዛዝ**

የስር ፍርድ ቤት መ/ቁ/53640፣መ/ቁ/284696 እና መ/ቁ/80361 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

መ/ዐ የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የመስማሚያ ሀሳብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ላይ የተመለከተው የችሎቱ ዳኛ የስራ ባልደረባዎቼ አመልካች ነሀሴ 21 ቀን 2000ዓ/ም የተደረገው ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ የይርጋ ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በደረሱበት መደምደሚያ የምስማማ ሲሆን ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ በተጠቀሰው ድንጋጌ እና ይህንን ተከትሎም በውሳኔው ላይ በተመለከተው የይርጋ ጊዜ ግን ያልተስማማሁ በመሆኑ የመስማሚያ ሀሳቤን እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ።

አመልካች ውሉ እንዲፈርስ በመጠየቅ ክሱን ያቀረቡት ውሉን አላውቀውም አልፈረምኩም ፤ ስምምነት አልሰጠሁም። በተጨማሪም ማንበብና መፃፍ ስለማልችል ፊርማው የኔ አይደለም በማለት ነው። ይህም የአመልካች ውል ይፍረስልኝ የዳኝነት ጥያቄ ከፈቃድ ጉድለት (Defect in consent) ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል። ይህ ከሆነ ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1810(1) የተመለከተው ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ የሚታሰበው

የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ በመሆኑ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ የሚገባው በዚሁ ድንጋጌ አግባብ ሊሆን ይገባል በማለት የመስማሚያ ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም